*በተለያዩ ቋንቋዎች ተዛማጅ መረጃዎችን ከሚከተሉት ቦታዎች ማግኘት ይቻላል*


**የማኒቶባ የሰርቪካል ነቀርሳ ማጣሪያ ፕሮግራም**
5 –25 Sherbrook St
Winnipeg, MB
R3C 2B1
1-866-616-8805
204-788-8626
www.cancercare.mb.ca/MCCSP/


•

**ቡክ ማርክ (Bookmark)**

ማንኛዋም ሴት ስለ ፓፕ ምርመራ ማወቅ ያለባት

•

**ትንንሽ መጽሔቶች**

*የፓፕ የምርመራ ውጤቶች – ማንኛዋም ሴት ማወቅ ያለባት*

*ምዝገባ (Registry) – እውነቶችና መረጃዎች/ዜናዎች*

•

**ቪዲዮ**

*የፓፕ ምርመራዎች – ማንኛዋም ሴት ማወቅ የሚያስፈልጋት*

*ኮልፖስኮፒ (Colposcopy)- – ማንኛዋም ሴት ማወቅ የሚያስፈልጋት*

*ማስታወሻ፤ ቪዲዮዎቹ ማኒቶባ ውስጥ በሚገኙት ቤተ መጽሐፍቶች ይገኛሉ::*

Amharic 05/08

## ክትባቱ ለማነው?

ክትባቱ እስካሁን በኤች ፒ ቪ ቫይረስ ላልተያዙ ሴቶች ነው::

ምንም እንኳን ወንዶች የብልት ኤች ፒ ቪ እንደሚኖርባቸው ቢታወቅም ክትባቱ ለወንዶች ይርዳ እንደሆን አይታወቅም:: የክትባቱ ዋና ዓላማ የሰርቢካል ነቀርሳን ለመቀነስ ነው::

## ክትባቱ ሁሉምን የኤች ፒ ቪ ዓይነቶች ሊከላከልልኝ ይችላል?

አይችልም:: ክትባቱ የተወሰኑ የኤች ፒ ቪ ዓይነቶችን ብቻ ነው ሊከላከልልዎ የሚችለው::

## በምክተብበት ወቅት በኤች ፒ ቪ ተይዤ የሆንኩ ከሆነስ?

ክትባቱ በኤች ፒ ቪ ተይዘው የነበሩ ከሆነ አያድንዎትም:: በክትባቱ ውስጥ ያለው ዓይነት ኤች ፒ ቪ ከሌለብዎ ክትባቱ ከእንደሱ ዓይነቱ ቫይረስ ይከላከልልዎታል::

## ክትባቱን የት ማግኘት እችላለሁ?

የጤና ባለሞያዎን ይጠይቁ::

## ከተከተብኩ በኋላም የፓፕ ምርመራዎችን ማድረግ አለብኝ?

አዎን:: መደበኛ የፓፕ ምርመራዎችን ማድረግ አለብዎ ምክንያቱም:-

- ክትባቱ ከሁሉም የኤች ፒ ቪ ዓይነቶች ሊከላከልልዎ አይችልም::
- በተከተቡበት ወቅት በኤች ፒ ቪ ተይዘው ሊሆን ይችላል::
- ክትባቱ ሙሉ መከላከያ ላይሆንዎት ይችላል::

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረጉ ሴቶች መደበኛ የፓፕ ምርመራዎችን ማድረግ ይኖርባቸዋል::

ብዙ ሴቶች በዓመት አንድ ጊዜ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት የፓፕ ምርመራ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል:: እነዚያ የምርመራ ውጤቶች ጥሩ ውጤት ካሳዩ የፓፕ ምርመራ የሚያስፈልግዎት በየሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል::

የሚቀጥለው የፓፕ ምርመራዎ መቼ እንደሆነ የጤና ባለሞያዎን ይጠይቁ::

## ኤች ፒ ቪ ካለብኝ ነቀርሳ ይኖረኛል ማለት ነው?

አይደለም:: አብዛኛውን ጊዜ ኤች ፒ ቪ ወደ ነቀርሳ አያመራም:: አንዳንድ የኤች ፒ ቪ ዓይነቶች ነቀርሳ ሊያስከትል ወደሚችል የሰርቪክስ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ::

መደበኛ የፓፕ ምርመራዎችን ማድረግ ይገባዎታል:: የፓፕ ምርመራዎች በማድረግ በኤች ፒ ቪ አማካኝነት የመጣን የሰርቪክስ ለውጦች ማወቅ ይቻላል::

ኤች ፒ ቪ በሌሎች የሰውነት ክፍሎችም ላይ ለውጦችን ሊያስከትል ይችላል:: ለምሳሌ በፊንጢጣ፤ በየወንዶች ብልት፤ በሴቶች ብልትና በአፍ ላይ:: ልክ እንደ ሰርቪክሱ በእነዚህ የሰውነት ክፍሎች ላይ የሚታዩት ለውጦች ወደ ነቀረሳ ሊያመራ ይችላል::

## የፓፕ ምርመራዬ ውጤት ጥሩ ባይሆንና የሰርቢክስ ሴሎቼ ለውጥ ቢታይባቸው ምን ይደረጋል?

ድጋሚ የፓፕ ምርመራ ወይም ልዩ ባለሞያ እንዲመረምርዎ ያስፈልግ ይሆናል:: ልዩ ባለሞያው ህክምና ያስፈልግ እንደሆነ ይወስናል:: በሰርቪክስ ላይ ለውጥ ከታየ በቶሎ ማከሙ የሰርቨክስ ነቀርሳን ሊከላከል ይችላል:: ውጤቱ ጥሩ ያልሆነ የፓፕ የምርመራ ከነበረብዎ ሁሉንም የምርመራ ቀጠሮዎችን አክበረው መገኘት ይኖርብዎታል::

# HPV

# ኤች ፒ ቪ የሰው ፓፒሎማ ቫይረስ

## *ስለ ብልት ኤች ፒ ቪ ሁሉም ሰው ማወቅ ያለበት*

የማኒቶባ የሰርቪክስ ነቀርሳ የማጣሪያ ፕሮግራም

CancerCare MANITOBA
*Action Cancer Manitoba*

Manitoba

*የማኒቶባ የሰርቪካል ነቀርሳ የማጣሪያ ፕሮግራም በማኒቶባ የነቀርሳ እንክብካቤ የሚካሄድ የማኒቶባ የጤና ፕሮግራም ነው*


*All translated materials completed in partnership with Sexuality Education Resource Centre*

## ኤች ፒ ቪ ምንድነው?

ኤች ፒ ቪ የሰው ፓፒሎማ ቫይረስ ነው፡፡ ከ100 በላይ የሚሆኑ የቫይረሱ ዓይነቶች ሰውን ሊያጠቁ ይችላሉ፡፡

## ምን ያደርጋል?

አንዳንድ የኤች ፒ ቪ ዓይነቶች በእጅና በእግር ላይ የሚታዩ ኪንታሮት ያስከትላሉ፡፡

ሌሎች የኤች ፒ ቪ ዓይነቶች (የብልት ኤች ፒ ቪ) በብልትዎ፤ በፊንጢጣዎ ወይም በሰርፊክስዎ ላይ ኪንታሮትን ያስከትላሉ፡፡

ሌሎች የኤች ፒ ኤ ዓይነቶች ደግሞ (የብልት) ወደ ሰርቪካል ነቀርሰ ሊያመራ የሚችል የሴርቪክስ ለውጥ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

እጅና አግር ላይ የሚወጣ ኪንታሮት የሚያስከትሉት ኤች ፒ ቪዎች ብልትዎን አያጠቁም፡፡

ብልቶችን የሚያጠቁ ኤች ፒ ቪዎች እጅዎንና እግርዎን አያጠቁም፡፡

## ኤች ፒ ቪ ምን ያህል የታወቀ  ነው?

ኤች ፒ ቪ በጣም የታወቀ ነው፡፡ በሕይወት ዘመናቸው ውስጥ ከ 4 ሰዎች 3ቱ ኤች ፒ ቪ ይይዛቸዋል፡፡ የተያዙት ሰዎች ሁሉ ግን የብልት ኪንታሮት ወይም የሰርቪክስ ለውጥ አያጋጥማቸውም፡፡

## በኤች ፒ ቪ እንዴት ልያዝ እችላለሁ?

በብልት፤ በፊንጢጣ እንዲሁም በአፍ በሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፤ ወይም በመተሻሸት በኤች ፒ ቪ በቀላሉ ሊያዙ ይችላሉ፡፡ የኤች ፒ ቪ ምልክቶችን ሳያዩ (ኪንታሮት፣ እብጠት የሰርቪካል ለውጥ) ኤች ፒ ቪን ሊያሰራጩ ይችላሉ፡፡

## ከኔ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ካለው ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ብፈጽም ስለ ኤች ፒ ቪ መጨነቅ ይኖርብኛል?

አዎን፡፡ ኤች ፒ ቪ ከማንኛውም የግብረ ሥጋ ባልደረባ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

## የብልት ኪንታሮት ቢኖርብኝ ወይም የሰርቪክሰ ሴሎቼ ለውጥ ቢያሳዩ፤ በመጨረሻውን የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸምኩት ሰው ኤች ፒ ቪ አለበት ማለት ነው?

ላይኖርበት ይችላል፡፡ በሕይወትዎ ውስጥ አንድ ጊዜ ቫይረሱ አጋጥሞታል ማለት ነው፡፡

## ኤች ፒ ቪ ማን እንዳስያዘኝ መናገር እችላለሁ?

አብዛኛውን ጊዜ መቼ ወይም ማን እንዳስያዘዎት መናገር በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

## ሳላውቀው ኤች ፒ ቪ ሊኖርብኝ ይችላል?

አዎን፡፡ ኤች ፒ ቪ በሰውነትዎ ውስጥ ኖሮ ለብዙ ዓመታት ላያውቁት ይችላሉ፡፡ በኤች ፒ ቪ ከተያዙ ከብዙ ዓመታት በኋላ ኪንታሮት ወይም የሰርቪክስ ለውጥ ሊከተል ይችላል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ለምን ኪንታሮት እንደሚኖርባቸውና ሌሎች ለምን እንደማይኖርባቸው አናውቅም፡፡

## ኢች ፒ ቪ እንዳለብኝ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ማኒቶባ ውስጥ የኤች ፒ ቪ ምርመራ በየጊዜው አይደረግም፡፡ የኤች ፒ ቪ ምርመራ በሚያደርጉበት ወቅት የኤች ፒ ቪ ዓይነት እንዳለብዎት ምርመራው ሊያሳይ ይችላል፡፡ ነገር ግን ምርመራው ቀደም ብሎ ኤች ፒ ቪ እንደነበረብዎ አያሳይም፡፡

ኤች ፒ ቪ በሰርቪክስ ላይ ያስከተለውን ለውጥ ለመረዳት ሴቶች የፓፕ ምርመራ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

እርስዎ ወይም የጤና ባለሞያዎ አንዳንድ ጊዜ የብልት ላይ ኪንታሮት ሊያዩ ይችላሉ፡፡ የብልት ላይ ኪንታሮት የአበባ ጎመን እምቡጥ ወይም እባጭ ሊመስል ይችላል፡፡

**ሴቶች** በብልታቸው ወይም በፊንጢጣቸው ውስጥና ውጭ እባጭ ወይም የሚያድግ ነገር ካዩ የጤና ባለሞያዎቻቸውን ማነጋገር ይገባቸዋል፡፡

**ወንዶች** በብልታቸውና በፊንጢጣቸው ላይ እባጭ ወይም የሚያድግ ነገር ካዩ የጤና ባለሞያዎቻቸውን ማነጋገር ይገባቸዋል፡፡

## ኮንዶም ኤች ፒ ቪን ሊከላከልልኝ ይችላል?

ኮንዶም በግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ ከብዙ በሽታዎች ሊከላከልልዎ ይችላል፡፡ ኮንዶም ከኤች ፒ ቪ ሁልጊዜ ላይከላከልልዎ ይችላል፡፡

## አደጋውን እንዴት መቀነስ እችላለሁ?

የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለማድረግ እርግጠኛው የመከላከያ መንገድ ነው ፡፡

የኤች ፒ ቪ ክትባት ያስፈልግዎ እንደሆነ የጤና ባለሞያን ይጠይቁ፡፡

የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በለጋ እድሜዎ አለማድረግ ወይም ማዘግየት፡፡

በወጣትነት በኤች ፒ ቪ መያዝ የሴቶችን በሰርቪካል ነቀርሳ የመያዝ ዕድል ከፍ ያደርገዋል

የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈጸሙ፤

- ሁል ጊዜ ኮንዶም ይጠቀሙ፡፡
- በሕይወት ዘመንዎ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያደርጓቸውን ሰዎች ቁጥር ይወስኑ፡፡
- ሰውነትዎ በሽታውን እንዲከላከል ጤናማና ጠንካራ አድርገው ያኑሩት፡፡ ጤና ሰጭ ምግቦችን ይመገቡ፤ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን ያድርጉ እንዲሁም ሰውነትዎ በቂ እረፍት ይኑረው፡፡
- የሲጋራ ጭስ የሴቶችን የሰርቪክስ ሴሎች ስለሚጎዱ ያስወግዱ፡፡

## ለብልት ኪንታሮት ሕክምናው ምንድነው?

የሚታዩ ኪንታሮቶችን ማከም ይቻላል፡፡ የሕክምና ባለሞያዎ ቆዳዎን በቢሮ ውስጥ ሊያክምዎ ይችላል ወይም እርስዎ እንዲያደርጉት መድሃኒት ሊያዝልዎ ይችላል፡፡

**ኪንታሮትን ለማከም ያለ ሃኪም ትዕዛዝ በመድሃኒት መሸጫ ሱቅ ውስጥ የሚሸጡትን መድሃኒቶች አይጠቀሙ፡፡ እነዚህ መድሃኒቶች በእጅና በእግር ላይ ለሚገኙ ኪንታሮቶች የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ እነዚህን መድሃኒቶች ቢጠቀሙ ለብልትዎ አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡**

## የብልት ኪንታሮት ካለብኝ በሰርቪካል ነቀርሳ የመያዝ ዕድሌ ከፍተኛ ነው ማለት ነው?

ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ የብልት ኪንታሮት ካለብዎ ቢያንስ አንድ ዓይነት ኤች ፒ ቪ አለብዎ ማለት ነው፡፡ የብልት ኪንታሮትን የሚያስከትለው ኤች ፒ ቪ የሰርቪካል ነቀርሳ የማስከተል ዕድሉ ዝቅ ያለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ነቀርሳውን በሚያስከትለው ኤች ፒ ቪ ተይዘው ሊሆን ይችላል፡፡

በሰርቪካል ነቀርሳ የመያዙን ዕድል ዝቅ ለማድረግ በየጊዜው የሚደረግ የፓፕ ምርመራ በጣም ጥሩ ዘዴ ነው፡፡

## ለኤች ፒ ቪ ፈውስ አለው?

የለውም፡፡ ለቫይረሱ ፈውስ የለውም፡፡ በኪንታሮቶቹና በቫይረሱ የተነሳ የተከተሉት የሰርቪክስ ለውጦች በራሳቸው ሊጠፉ ይችላሉ ወይም በሕክምና ሊጠፉ ይችላሉ፡፡

## ለኤች ፒ ቪ ክትባት አለ?

አዎን፤ ለአንዳንድ የኤች ፒ ቪ ዓይነቶች በካናዳ ውስጥ ክትባት አለ፡፡